የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ

የእርምጃ አወሳሰድ እና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ

ቁጥር....፪ሺ፲፰

የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ በድሬዳዋ አስተዳደር ውስጥ የሚያከናወነውን ቁጥጥር የሚደረግባቸው ምርቶች ቁጥጥር ስራን ማጠናከር የማህበረሰቡን ጤና ለመጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በአስተዳደሩ ውስጥ ህገ-ወጥ ምርት፣ ደህንነቱና ጥራቱ ያልተጠበቀ ምርት ምክንያት ለማህበረሰብ ጤና ስጋት አሳሳቢ ጉዳይ በመሆኑ፤

በፌደራል ደረጃ የወጣውን የምግብና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፻፲፪/፪ሺ፲፩ እና የድሬዳዋ አስተዳደር የምግብ መድሃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ደንብ ቁጥር ፴፫/፪ሺ፲፰ በዝርዝር ለማስፈጸም መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአስተዳደሩ ባለስልጣን ቁጥጥር በሚደረግበት ምርት ወይም ሰው ላይ የሚወሰድ አስተዳደራዊ ቅጣትና እርምጃ አግባብ ያለውን ህግ መሰረት ያደረገ እንዲሆን እና ቁጥጥር የሚደረግበት ሰው አግባብ በሌላቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎች ምክንያት ያደረበትን ቅሬታ ማቅረብ የሚችልበትን እና ማስተካከያ የሚያገኝበትን ስነ-ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የአስተዳደሩ ጤና ቢሮ በድሬዳዋ አስተዳደር የምግብና መድኃኒት አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፴፫/፪ሺ፲፭ አንቀጽ ፸፯ መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል::

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

፩፥ አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "አስተዳደራዊ ቅጣትና እርምጃ አወሳሰድ እና ቅሬታ አቀራረብ መመሪያ ቁጥር ..../፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪፥ ትርጉም

በፌደራል ምግብ እና መድሃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፻፲፪/፪ሺ፲፩ እና በድሬዳዋ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፴፫/፪ሺ፲፭ ውስጥ የተሰጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ

፩፥ "አስተዳደር" ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ነው፡፡

፪፥ "አዋጅ" ማለት የኢፌዲሪ የምግብ እና የመድሃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፻፲፪/፪ሺ፲፩ ነው፡፡

፫፥ "ደንብ" ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ምግብ እና የመድሃኒት አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፴፫/፪ሺ፲፭ነው፡

Dire Dawa Administration Health Bureau
Administrative Actions and Grievance Handling and Complaint Submission Directive No. …../2026

The Dire-Dawa Administration Food, Medicine, and Health Control Authority is working to strengthen the regulation of products within the Dire-Dawa Administration to ensure public health. This is essential for safeguarding the well-being of the community.

The presence of illegal, unsafe, and substandard products within the administration poses a significant risk to public health. This has become a pressing issue that needs to be addressed.

To enforce the Federal Food and Medicine Administration Proclamation No. 1112/2019 and the Dire-Dawa Administration Food and Medicine Administration and Control Regulation No. 33/2015 in detail, it is necessary to issue directive.

The administration's regulatory authority must ensure that any administrative penalties or actions taken against products or individuals are based on the law. Additionally, individuals subject to regulation should have the opportunity to present complaints and seek corrections if they face inappropriate administrative actions.

In accordance with Article 77 of the Dire-Dawa Administration Food and Medicine Administration Regulation No. 33/2015, the administration's authority has issued this directive.

Part One:
General

1. Short Title

This directive may be cited as the "Administrative Actions and Grievance Handling and Complaint Submission Directive No. …../2026."

2. Definitions

The definitions provided in the Federal Food and Drug Administration Proclamation No. 1112/2011 and the Dire Dawa Administration Regulation No. 33/2026 shall remain applicable unless the context otherwise requires.

In this directive:

1) "Administration" refers to the Dire Dawa Administration.
2) "Proclamation" refers to the Federal Food and Drug Administration Proclamation No. 1112/2019.
3) "Regulation" refers to the Dire Dawa Administration Food and Drug Administration Regulation No. 33/2022.

፬፥ “የአስተዳደሩ ጤና ቢሮ” ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ ነው

፭፥ “የአስተዳደሩ ባለስልጣን” ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር የምግብ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ ባለስልጣን ነው

፮፥ “የፌዴራል ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ የምግብና መድሃኒት ባለስልጣን ነው

፯፥ “ኢንስፔክተር” ማለት ለአስተዳደሩ ባለስልጣን በዚህ ደንብ የተሰጠውን የቁጥጥር ሥልጣንና ተግባር ለመፈጸም የሚመደብ ባለሙያ ነው

፰፥ “ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት” ማለት ምግብ፣ መድሃኒት፣ የህክምና መሣሪያ፣ የውበት መጠበቂያ፣ ትምባሆ እና በአዋጁ እና ደንቡ መሠረት የተካተቱ ሌሎች ምርቶችን ያጠቃልላል፤

፱፥ “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት በወጣው ደረጃ መሰረት ቁጥጥር የሚደረግበትን ምርት አገልግሎት አቅራቢ ወይም የንግድ ሥራ ለሚሰማራ ሰው ወይም ተቋም የሚሰጥ እውቅና ነው

፩፥ “ምግብ ማበልጸግ” ማለት በማህበረሰቡ ወይም በማህበረሰቡ የተወሰነ ክፍል የሚታይን የአንድ ወይም የብዙ ንጥረ ምግቦች እጥረትን ለመከላከል ወይም ለመተካት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ንጥረ ነገሮችን በምግብ ውስጥ መጨመር ነው፣

፲፩፥ የምግብ ጭማሪ” ማለት አግባብ ባለው የደህንነት መስፈርት መሠረት ተዘጋጅቶ ምግብን ለማጣፈጥ፣ ለማቅለም፣ ሳይበላሽ ለማቆየት፣ ለማሳመር ወይም ለተመሳሳይ ሌላ ዓላማ በምግብ ላይ የሚጨመር ንጥረ-ነገር ነው፤

፲፪፥ “አስተዳደራዊ ቅጣት” ማለት የአስተዳደሩ ባለስልጣን ቁጥጥር የሚደረግበትን ምርት አገልግሎት የሚያቀርብ ወይም ወይም የንግድ ሥራ በሚሰማራ ሰው ወይም ተቋም ላይ የሚወሰን የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤ የብቃት ማረጋገጫ ወይም የገበያ ፈቃድ ወይም ልዩ ፈቃድ ማገድ፣ መሰረዝ፤ በጥቁር መዝገብ መመዝገብ፤ ምርቱን መውረስ፤ ምርቱን ከተሰራጨበት እንዲሰበሰብ ወይም ምርቱ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለዘለቄታው ለገበያ ወይም ለአገልግሎት እንዳይቀርብ ማድረግ፣ የገንዘብ መቀጮ መጣል እና ተመሳሳይ እርምጃዎችን የሚያካትት ይሆናል፤

፲፫፥ “የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ” ማለት የአስተዳደሩ ባለስልጣን በቁጥጥር ወቅት ያገኛቸውን የህግ ጥሰቶችን እና ይህንኑ ከቁጥጥር ህግ ጋር የተጣጣመ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ማስተካከያዎችን በተመለከተ ቁጥጥር የሚደረግበትን ምርት አገልግሎት አቅራቢ ወይም የንግድ ሥራ ለሚሰማራ ሰው ወይም ተቋም ለማሳወቅ የሚሰጥ የፅሁፍ ግንኙነት ነው፤

፲፬፥ “ስረዛ” ማለት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን መሰረዝና በአዋጁ እና ደንቡ መሰረት ቁጥጥር የሚደረግበትን ምርት አገልግሎት አቅራቢ ወይም የንግድ ሥራ ለሚሰማራ ሰው ወይም ተቋም ላይ እንዳይሰማራ ፈቃድን መሰረዝ ነው፤

፲፭፥ “እገዳ” ማለት የአስተዳደሩ ባለስልጣን ለእገዳ የሚያበቃ ጥፋት መኖሩ ሲያረጋግጥ ቁጥጥር የሚደረግበትን ምርት አገልግሎት አቅራቢ ወይም የንግድ ሥራ ለሚሰማራ ሰው ወይም ተቋም እንዳይሰማራ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ለተወሰነ ጊዜ ለማገድ የሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ነው፤

4) ‘’Administration Health Bureau’’ refers Dire Dawa administration health bureau
5) "Administrative Authority" refers to the Dire Dawa Administration Food, Drug, and Health Care Authority.
6) "Federal Authority" refers to the Ethiopian Food and Drug Authority.
7) "Inspector" refers to a professional assigned by the administrative authority to perform control and regulatory functions as provided by this regulation.
8) "Controlled Product" includes food, drugs, medical devices, cosmetics, tobacco, and other products specified under the proclamation and regulation.
9) "Certificate of Competence" refers to the recognition granted to a person or entity providing services or engaged in trade related to controlled products, based on established standards.
10) "Food Fortification" refers to the addition of one or more nutrients to food to prevent or correct deficiencies observed in the community or a specific segment of the community.
11) "Food Additive" refers to a substance added to food to enhance its appearance, flavor, preservation, or for similar purposes, prepared in accordance with safety standards.
12) "Administrative Penalty" includes written warnings, suspension or revocation of certificates or market permits, blacklisting, product recall, temporary or permanent market withdrawal, financial penalties, and similar actions imposed by the administrative authority on individuals or entities providing services or engaged in trade related to controlled products.
13) "Warning Letter" refers to a written communication issued by the administrative authority to a service provider or trader regarding violations found during inspections and necessary corrective actions.
14) "Revocation" refers to the cancellation of a certificate of competence or permit issued to a service provider or trader under the proclamation and regulation.
15) "Suspension" refers to the temporary withholding of a certificate of competence by the administrative authority when a violation justifying suspension is confirmed.

፲፮፥ “ጥቁር መዝገብ” ቁጥጥር የሚደረግበትን ምርት አገልግሎት አቅራቢ ወይም የንግድ ሥራ ለሚሰማራ ሰው በህገ ወጥ ድርጊት ውስጥ ተሳትፎ ሲኖረው ጥፋት ፈጻሚው በተመሳሳይ ስራ እንዳይሰማራ ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲሁም ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ መያዥያ ስርዓት ነው

፲፯፥ “ቅሬታ" ማለት አስተዳደራዊ ቅጣት የተወሰደበት ማንኛውም ሰው በአስተዳደሩ ባለስልጣን በወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ በጽሁፍ የሚያቀርበው አቤቱታ ነው፤

፲፰፥ “ቅሬታ መስማት" ማለት ማንኛውም ሰው በአስተዳደሩ ባለስልጣን በወሰደው አስተዳደራዊ እርምጃ ላይ የሚያቀርበው ቅሬታ የሚስተናገድብት መንገድ ነው፤

፲፱፥ "የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ" ማለት በአስተዳደሩ ባለስልጣን በተወሰደው የአስተዳደራዊ እርምጃ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው የሚያቀርበውን ቅሬታ ለመስማት እና ለመመርመር በአስተዳደሩ ባለስልጣን የተቋቋመ አካል ነው

፳፥ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፩፥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

፫፥ የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአስተዳደሩ ውስጥ በሚቀርብ ወይም በሚመረት ቁጥጥር በሚደረግበት ምርት፤ ቁጥጥር የሚደረግበትን ምርት ለአገልግሎት የሚያቀርብ ወይም የንግድ ሥራ በሚሰማራ ሰው ወይም ተቋም ላይ በፌደራል ምግብ እና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፻፲፪/፪ሺ፲፩ እና በድሬዳዋ አስተዳደር የምግብ እና መድሃኒት አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፴፫/፪ሺ፲፭ እና እነዚህን ተከትለዉ በሚወጡ መመሪያወች የተደነገጉት ድንጋጌዎች አተገባበር ጋር በተያያዘ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

አስተዳደራዊ እርምጃ

፬፥ አስተዳደራዊ እርምጃ ስለሚሰጥበት ሁኔታ

፩፥ በዚህ መመሪያ የተካተተ፣ በአዋጁና ደንቡ እንዲሁም እነሱን ለማስፈፀም በወጡ መመሪያዎች ላይ የተመለከቱ ክልከላዎችን በመተላለፍ ወይም ቁጥጥር በሚደረግባቸው ምርቶችን አስመልክቶ በወጣ አገራዊ የደረጃ መስፈርት ባለሟሟላት እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች ለሚፈጸም ጥፋት አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወስድ ይሆናል፡፡

፪፥ የአስተዳደሩ ባለሰልጣን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የተለያዩ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን በአንድ ላይ አጣምሮ ሊወስድ ይችላል

፫፥ ባለስልጣኑ አስተዳደራዊ ቅጣት የሚጥለው በቅድሚያ አስተዳደራዊ እርምጃ የሚያስወስድ ጥፋት መፈጸሙን አግባብነት ያለውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ በማረጋገጥ ይሆናል፡፡

፬፥ የአስተዳደሩ ባለስልጣን አስተዳደራዊ ቅጣት ከመጣሉ በፊት ጥፋት ስለመፈጸሙ ክስ የቀረበበት ሰው በ2 የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ እንዲሰጥ እና ማስረጃ ካለው እንዲያቀርብ ዕድል ይሰጠዋል

16) "Blacklist" refers to a system of recording information to prevent and control individuals or entities involved in illegal activities related to controlled products, ensuring strict monitoring and supervision.
17) "Complaint" refers to a written appeal submitted by any person against an administrative penalty imposed by the administrative authority.
18) "Complaint Hearing" refers to the process by which a complaint submitted against an administrative action is heard.
19) "Complaint Hearing Committee" refers to a body established by the administrative authority to hear and investigate complaints against administrative actions.
20) "Person" refers to a natural person or a legal entity recognized by law.
21) Any reference to the male gender shall include the female gender.

3. Scope of Application

This directive shall apply to products controlled or manufactured within the administration, as well as to individuals or entities providing services or engaged in trade related to controlled products, in accordance with the Federal Food and Drug Administration Proclamation No. 1112/2019, the Dire Dawa Administration Food and Drug Administration Regulation No. 33/2022, and subsequent directives issued thereafter.

Part Two:

Administrative Measures

4. Imposition of Administrative Measures

1) Administrative measures will be taken for violations related to the restrictions outlined in this directive, the proclamation, the regulation, and the directives issued to enforce them, as well as for products subject to control or restriction, in accordance with the national standards and other relevant laws.
2) The administrative authority may combine various administrative measures if deemed appropriate.
3) The imposition of administrative penalties will be based on verified evidence of the violation, following prior administrative action.
4) Before imposing an administrative penalty, the person accused of the violation will be given 2 working days to respond and present evidence.

፭፥ አስተዳደራዊ ክስ የቀረበበትን ሰው በአድራሻው ማግኘት ያልተቻለ ወይም በንኡስ አንቀጽ (፪) መሰረት ምላሽ እንዲያቀርብ ዕድል በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ያላቀረበ እንደሆነ ክሱን የሚመለከተው የአስተዳደሩ ባለስልጣን የስራ ክፍል አግባብ ነው ያለውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፮፥ የአስተዳደር ባለስልጣን የቃል ማስጠንቀቂያ፣ ቀላል የገንዘብ ቅጣት ፣ ከባድ የገንዘብ ቅጣት ፣እገዳ ፣ ስረዛ እና ጥቁር መዝገብ ማስፈሪያ ቅጣቶችን ማስረጃዎችን መሰረት በማድረግ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

፯፥ የአስተዳደሩ ባለስልጣን ከሌላ አስተዳደራዊ እርምጃ ጋር ወይም በተናጠል የገንዘብ ቅጣት ሊጥል ይችላል

፰፥ የአስተዳደሩ ባለስልጣን የስራ ክፍል በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ሰው በአዋጁ አንቀጽ ፷፮ እና በደንቡ አንቀፅ ፶፱ መሰረት ቅሬታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡

፭፥ የቃል ማስጠንቀቂያ ስለሚሰጥበት ሁኔታ

፩፥ ማንኛዉም በአስተዳደሩ ውስጥ በሚቀርብ ወይም በሚመረት ቁጥጥር የሚደረግበት ምርትን ለአገልግሎት የሚያቀርብ ወይም የንግድ ሥራ ላይ በሚሰማራ ሰው ወይም ተቋም የወጡ መስፈርቶችን መሰረት አስገዳጅ መስፈርቶችን አሟልቶ ሌሎች መስፈርቶች ላይ ጉድለት አሳይቶ ከተገኘ

፪፥ በቁጥጥር ወቅት በጉድለት ማሳወቂያ ቅፅ ወይም መተማመኛ የተቀመጠው ፎርም ተሞልቶ ከተሰጠ እንደ ቃል ማስጠንቀቂያ ተደረጎ ይቆጠራል

፮፥ ፅሁፍ ማስጠንቀቂያ (ቀላል ቅጣት) ስለሚሰጥበት ሁኔታ

፩፥ የቃል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በዓመት ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የቃል ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው

፪፥ በባለስልጣኑና አግባበብ ያላቸው አካለት ባወጡት መስፈርት ውስጥ የአስገዳጅ መስፈርቶች ጉድለት አሳይቶ ከተገኘ

፫፥ የአስተዳደሩ ባለስልጣን እንደ ጥፋቱ ዓይነት የተወሰኑ የአገልግሎት ክፍሎችን በጊዜያዊነት ሊያሽግ ወይም አገልግሎት እንዳይሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፬፥ የአስተዳደሩ ባለስልስልጣን በዚህ መመሪያ መጨረሻ አባሪ በተደረገው የፅሁፍ ማስጠንቂያ (የቀላል ቅጣት) ሰንጠረዥ ውስጥ የተካተቱ የገንዘብ ቅጣቶችና እና ሌሎች ተዛማች ቅጣቶች ይቀጣል፡፡

፯፥ ከባድ ቅጣት (የብቃት ማረጋገጫ ወይም ምዝገባ ምስክር ወረቀት ዕገዳ) ስለሚሰጥበት ሁኔታ

፩፥ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ (ቀላል ቅጣት) ተላልፎበት በዓመት ውስጥ በድጋሚ የፈፀመ የቀላል የገንዘብ ቅጣቱን እጥፍ እና የ፭ ቀን እገዳ

፪፥ ከአስተዳደሩ ባለስልጣን ሳያሳውቅ/ሳያስፈቅድ ተቋሙ የቦታ አድራሻ ላይ ለዉጥ ካደረገ 7 ቀን እገዳ

፫፥ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን በህገ ወጥ መንገድ ለሌላ ሶስተኛ ወገን ካስተላለፈ ፲ ቀን እገዳ

፬፥ ባለሥልጣኑ በድርጅቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ለሚያደርጋቸው ማንኛውም የኢንስፔክሽን ስራዎች እንቅፋት የፈጠረ እንደሆነ፤ ፲፭ ቀን እገዳ የአስተዳደሩ ባለስልስልጣን በከባድ ቅጣት (የብቃት ማረጋገጫ ወይም ምዝገባ ምስክር ወረቀት እገዳ) ሰንጠረዥ

5) If the accused cannot be located or fails to respond within the given time, the relevant administrative authority will issue a decision based on the case.
6) The administrative authority may impose measures such as verbal warnings, minor fines, heavy fines, suspension, revocation, or blacklisting, based on evidence.
7) The administrative authority may impose a financial penalty in addition to or separately from other administrative measures.
8) A person dissatisfied with the decision of the administrative authority may appeal under Article 66 of the proclamation and Article 59 of the regulation.

5. Verbal Warnings

1) A verbal warning will be issued to any person or entity providing or engaging in trade with controlled products if they fail to meet mandatory standards while complying with other requirements.
2) If a gap notices or acknowledgment form is issued during inspection, it will be considered a verbal warning.

6. Written Warnings (Minor Penalties)

1) A written warning will be issued if a verbal warning has been given twice within a year.
2) If mandatory standards are not met as per the requirements set by the authority.
3) The administrative authority may temporarily suspend certain service units or services based on the nature of the violation.
4) The administrative authority will impose fines and other penalties as outlined in the attached table of written warnings (minor penalties).

7. Severe Penalties (Suspension of Certification or Registration)

1) If a minor financial penalty is imposed again within a year after a written warning, the penalty will be doubled, and a 5-day suspension will be applied.
2) If an institution changes its address without notifying the authority, a 7-day suspension will be imposed.
3) If a certification document is illegally transferred to a third party, a 10-day suspension will be imposed.
4) If an institution obstructs inspection activities at any time, a 15-day suspension will be imposed.

ውስጥ የተካተቱ የገንዘብ ቅጣቶችና እና ሌሎች ተዛማች ቅጣቶች ይቀጣል፡፡

፰፡ የብቃት ማረጋገጫ ስረዛ ስለሚደረግበት ሁኔታ

፩፡ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተገኘው በሐሰተኛ ሰነድ ወይም በተጭበረበረ መንገድ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

፪፡ ድርጅቱ በባለስልጣኑ የተጣለበትን እገዳ በመተላለፍ ስራውን ከቀጠለ፤ለ ፩ ወር የ፭ሺ ብር መቀጮ

፫፡ ድርጅቱ ወይም ተቋሙ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ የእግድ ወይም ከባድ ቅጣት የተወሰደበት ከሆነ ለ ፮ ወር የ፲ሺ ብር መቀጮ

፬፡ ቁጥጥር በሚደረግበት ተቋም/ምርት የተቀመጡትን መስፈርቶች ባለማሟላቱ በሰው ጤና ወይም አካል ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሎ ከተገኘ ወይም የምርቱ የደረጃ ጉድለት በሰው ጤና ወይም ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ዓይነት ከሆነ ፴ሺ እና ለ፩ ዓመት ስረዛ

፭፡ ቁጥጥር በሚደረግበት ተቋም/ምርት የተቀመጡትን መስፈርቶች ባለማሟላቱ በሰው ጤና ወይም አካል ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሎ ከተገኘ ወይም የምርቱ የደረጃ ጉድለት በሰው ወይም አካል ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሎ ከተገኘ ወይም የምርቱ የደረጃ ጉድለት በሰው ጤና ወይም ሕይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሎ ከሆነ ፷ሺ እና ለ፫ ዓመት ስረዛ

፮፡ ቁጥጥር በሚደረግበት ተቋም/ምርት የተቀመጡትን መስፈርቶች ባለማሟላቱ በሰው ጤና ወይም አካል ላይ በፈጠረው ጉዳት ሞት አስከትሎ ከተገኘ የ፻ ሺ ብር መቀጮ እና የ፭ ዓመት ስረዛ

፱፡ ጥቁር መዝገብ ስለማስፈር

ድርጅቱ ለሁለተኛ ጊዜ ስረዛ የተከናወነበት ለ፭ ዓመት ጥቁር መዝገብ ውስጥ ይካተተል

፲፡ ምርት ስለመውረስ

፩፡ የአስተዳደሩ ባለስልጣን ከሌሎች አስተዳደራዊ ቅጣቶች በተጨማሪ ከተፈጸመው ጥፋት ጋር በተያያዘ ያለውን ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት በራሱ ውሳኔ ወይም በፍርድ ቤት ሲወሰን ለመውረስ ይችላል፡፡

፪፡ ምርት ለመውረስ ከመወሰኑ በፊት የጥፋቱን ዓይነት፣ ያደረሰውን ወይም ሊያደርስ ይችል የነበረውን ጉዳት፣ የጥፋት ፈጻሚው ከጥፋቱ የመታረም ፈቃደኝነት፣ ድርጅቱ ለማህበረሰቡ ያለውን አውንታዊ አስተዋጽዎና መሰል ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡

፫፡ በዚህ መመሪያ መሰረት የተወረሰ ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት አገልግሎት ላይ እንዲውል ወይም እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

፬፡ የአስተዳደሩ ባለስልጣን የወረሰው ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት አገልግሎት ላይ መዋል የሚችል እንደሆነ ምርቱ ተሸጦ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ወይም ምርቱ ለበጎ አድራጎት ዓላማ እንዲውል ሊወስን ይችላል፡፡

The administrative authority will impose fines and other penalties as outlined in the attached table of severe penalties.

8. Revocation of Certification

1) If a certification document is obtained through false or fraudulent means.
2) If an institution continues operations despite a suspension, a fine of 5,000 birr and a 1-month suspension will be imposed.
3) If an institution receives a second suspension or severe penalty within a year, a fine of 10,000 birr and a 6-month suspension will be imposed.
4) If a controlled institution/product fails to meet standards, causing significant harm to health or life, a fine of 30,000 birr and a 1-year suspension will be imposed.
5) If a controlled institution/product fails to meet standards, causing severe harm to health or life, a fine of 60,000 birr and a 3-year suspension will be imposed.
6) If a controlled institution/product fails to meet standards, resulting in death, a fine of 100,000 birr and a 5-year suspension will be imposed.

9. Blacklisting

The organization has been revoked for the second time and will be listed on the blacklist for 5 years.

10. Product Recall

1) In addition to other administrative penalties, the responsible authority may decide to recall a product if it is found to be defective, either voluntarily or through a court order.
2) Before deciding to recall a product, the following factors will be considered: the nature of the defect, the harm caused or potential harm, the willingness of the responsible party to rectify the issue, the organization's positive contributions to society, and similar circumstances.
3) Products subject to recall under this directive will either be allowed to remain in service or be removed from the market.
4) The responsible authority may decide that a recalled product can remain in service if it is sold for government revenue or used for charitable purposes.

፭፥ በማንኛውም አካል የተወረሰውና መወገድ ያለበት ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት ምርቱ ባለቤት ወይም በተያዘበት ሰው ወጪ የሚወገድ ይሆናል፡፡

፮፥ የአስተዳደሩ ባለሰልጣን በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሰረት በሚከተሉት ሁኔታዎች ምርትን በቀጥታ ለመውረስ ይችላል፡-

ሀ) ምርቱ መመዝገብ ወይም ዕውቅና ሊኖረው የሚገባ ሆኖ እያለ ያልተመዘገበ ወይም ዕውቅና ያልተሰጠው ምርት፤

ለ) የብቃት ማረጋገጫ ወይም ልዩ ፈቃድ ወይም የገበያ ፈቃድ ሳይኖረው ወይም ሐሰተኛ የብቃት ማረጋገጫ ወይም ልዩ ፈቃድ ወይም የምዝገባ ፈቃድ ወይም ዕውቅና በመያዝ የሰራ፣

ሐ) ተመሳስሎ የተሰራ ምርት፤

መ) የምርቱን ምንጭ ወይም ህጋዊ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሰነድ በአስተዳደሩ ባለሰልጣን በሚጠየቅበት ወቅት ወይም እንዲያቀርብ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ማቅረብ ያልቻለ፤

ሠ) በህግ የሚጠየቁ እንደ የጤና ማስጠንቀቂያ፣ አስገዳጅ ምልክት እና መሰል መስፈርቶችን የተላለፈ፤

ረ) ሊታይ የሚችል ብልሽት ያለው ምርት እንደሆነ

ሰ) የመጠቀሚያ ጊዜው ያለፈ ወይም የመጠቀሚያ ጊዜ ሊኖረው የሚገባ ምርት ሆኖ የመጠቀሚያ ጊዜ የሌለው ወይም የማይታይ ምርት እንደሆነ፤

ሸ) ማስታወቂያ፣ ፕሮሞሽን እና ስፖንሰርሺ ክልከላን በመተላለፈ ማስታወቂያ፣ ፕሮሞሽን ወይም ስፖንሰርሺፕ የተሰራበት ቁጥጥር የሚደረግበት ምርት፣ መሳሪያ ወይም ቁስ ፤

ቀ) ለገበያ ወይም ለአገልግሎት እንዳይቀርብ የተከለከለ ምርት፤

በ) ከተፈቀደለት ደረጃ በላይ ምርት የያዘ

፲፩፥ አስተዳደራዊ እርምጃ እና ቅጣት አፈፃፀም

በወንጀል ህግ እና በሌሎች ህጎች የተመለከተው ኃላፊነትና ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን መመሪያ የጣሰ ማንኛውም ሰው፡- እንደጥፋቱ ሁኔታ ድርጊቱን የማስቆም፣ የማዘጋት፣ የማሸግ እና ምርት መውረስ እንዲሁም የማስነሳት እርምጃ በአስተዳደሩ ባለስልጣን አማካይነት ይወሰድበታል፡፡ በዚህም መሰረት

፩፥ የባለስልጣኑ ተቆጣጣሪዎች ማስረጃን መሰረት በማድረግ የቃል ማስጠንቀቂያ እና ቀላል ቀላል ቅጣት ውስጥ የተካተቱ የአስተዳራዊና የቅጣት መቀጮችን ቀጥታ ይወስናሉ

፪፥ የባለስልጣኑ ተቆጣጣሪዎች ማስረጃን መሰረት በማድረግ በከባድ በስረዛ በእግድ እና በጥቁር መዝገብ የተካተቱ የቅጣት ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ ለባለስልጣኑ ያቀርባሉ፡፡ ባቀረቡት ውሳኔና ማስረጃ መሰረት ባለስልጣኑ አስተዳራዊ ወይም ቅጣት መሰርት ውሳኔውን ያሳውቃል፡፡

፫፥ በዚህ መመሪያ መሠረት ቅጣት የተወሰነበት ማንኛውም ሰው በባለስልጣኑ የተሰጠውን የቅጣት ወረቀት በመያዝ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ አለበት፡

፬፥ በዚህ ክፍል ቁጥር ፪ መሠረት መቀጫውን በተጠቀሰ ጊዜ ገቢ ያላደረገ ሰው የተጣለበትን ቅጣት መጠን የሚከፍለው እጥፍ በማድረግ ነው

፲፪፥ የወንጀል ክስ ስለመምራት

፩፥ በዚህ መመሪያ የተመለከተን ገደብ፣ መስፈርት፣ ሃላፊነትና ክልከላ ተግባር በፌደራል አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፻፲፪/፪ሺ፲፩ በወንጀል ህጉ ተሸፍኖ ያለ ተግባር እንደ ተግባሩ አግባብነት በእነዚህ ህጎች መሰረት በወንጀል ተጠያቂነት ይኖራል

5) Any product that is recalled and must be removed from the market will be disposed of at the expense of the product owner or the person in possession of it.
6) The responsible authority may directly recall a product under the following circumstances:
    a) A product that should have been registered or certified but was not;
    b) A product manufactured without the necessary certification, special permit, or market authorization, or with falsified documents;
    c) A counterfeit product;
    d) A product for which the source or legality cannot be verified when requested by the authority;
    e) A product that violates health warnings, mandatory labels, or similar legal requirements;
    f) A product with visible defects;
    g) A product with an expired or missing expiration date;
    h) A product that violates advertising, promotion, or sponsorship regulations;
    i) A product prohibited from being sold or serviced;
    j) A product that exceeds permitted levels.

11. Administrative Actions and Penalties

In addition to criminal liability and penalties under criminal law and other laws, any person who violates this directive will be subject to administrative actions, including suspension, closure, seizure, product recall, and other measures by the responsible authority. Specifically:

1) The authority's inspectors will issue verbal warnings and minor penalties based on evidence.
2) The authority's inspectors will recommend severe penalties, including suspension, fines, and blacklisting, to the responsible authority, which will then issue the final decision.
3) Any person penalized under this directive must pay the fine within one month of receiving the penalty notice.
4) If the fine is not paid within the specified time, the penalty amount will be doubled.

12. Criminal Charges

1) Any violation of the limits, requirements, responsibilities, or prohibitions outlined in this directive, as covered under Federal Proclamation No. 1112/2011 and the Criminal Code, will be subject to criminal liability.

፪፡ ባለስልጣኑ ለሚመለከተው የመንግስት አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሰረት ጉዳይ የወንጀል ህግ ሲጣስ መረጃ በማጠናቀርና የወንጀል ክስ እንዲመሰረት በመምራት አግባብ ካላቸው የመንግስት/የህግ ክፍል ጋር በጋራ ይሰራል፡

፫፡ የመንግስት/የህግ ክፍል የተላከለትን ጉዳይ በአግባቡ ከመረመረ በኋላ የወንጀል ህግ እንደተጣሰ ሲያምንና ጉዳዩን በፍርድ ቤት ለመደገፍ ማስረጃ ሲኖረው ማንኛውም ጉደይ ክስ እንዲመሰረትበት አግባብ ላለው የክልል ወይም ፌዴራል አቃቤ ህግ ያስተላልፋል፡

፬፡ የመንግስት/የህግ ክፍል የመጨረሻ የፍርድ ቤት ውሳኔን ለባለሰልጣኑ ያስታውቃል፡

፭፡ የመጨረሻ የፍርድ ቤት ውሳኔ ሪከርድ ለአስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ እንዲረዳ በአግባባቡ ያስቀምጣል

፮፡ ባለስልጣኑ አግባብ ባለው ሚዲያ የተወሰደውን እርምጃ ህብረተሰቡ እንዲያውቀው ይደረጋል

ክፍል ሶስት

ስለ ቅሬታ ሰሚ አካል መቋቋም፣ አደረጃት እና ተግባርና ኃላፊነት

፲፫፡ ስለቅሬታ ሰሚ አካል መቋቋም

፩፡ በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፻፲፪/፪ሺ፲፩ አንቀጽ ፵፱ (፩) እና በደንብ ቁጥር ፴፫/፪ሺ፲፭ መሠረት ባለሥልጣኑ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ ኮሚቴ እየተባለ የሚጠራ) በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

፪፡ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ ይሆናል፡፡

፲፬፡ ዓላማ

የኮሚቴው ዓላማ ቁጥጥር በሚደረግባቸው ተቋማት ላይ የተወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በማየት፣ ሕጋዊና ፍትሃዊ ውሳኔ እንዲሰጥ ማድረግ ነው፡፡

፲፭፡ የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

ኮሚቴው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩፡ የተወሰደውን አስተዳደራዊ እርምጃ ላጸደቀው የሥራ ክፍል የቀረበበትን ቅሬታ እንዲያውቀውና ለቀረበው ቅሬታ በጽሁፍ መልስ እንዲያቀርብ ያደርጋል፤

፪፡ በተወሰደ አስተዳደራዊ እርምጃ የቀረበ ቅሬታን ይሰማል፣ ይመረምራል፣ ውሳኔም ይሰጣል፤

፫፡ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስፈልጉትን ማንኛውንም የሰነድ፣ ማስረጃ ወይም ምስክር እንዲሁም የኢንስፔክሽን ሪፖርት እንዲቀርብለት ያደርጋል፤

፬፡ ኮሚቴው የሚቀርብለትን ማንኛውም ቅሬታ አግባብነት ካላቸው አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ጋር በማገናዘብ መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤

፭፡ የአስተዳደራዊ እርምጃ ውሳኔ ሊያፀና፣ ሊያሻሽል ወይም ሊለውጥና ለውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆነ ተያያዥነት ያለው ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ኮሚቴው ውሳኔን ለማጽናት፣ ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ የተጠቀመበትን የሕግ መሰረት በውሳኔው ውስጥ ማመልከት አለበት፤

2) The authority will collaborate with the relevant government body to compile information and initiate criminal charges if a violation of criminal law is suspected.
3) The government/legal body will review the case and, if convinced that a criminal violation has occurred, will forward the case to the appropriate regional or federal prosecutor for legal action.
4) The government/legal body will inform the authority of the final court decision.
5) The final court decision will be recorded to assist in further administrative actions.
6) The authority will inform the public through appropriate media about the actions taken.

Part Three:

Establishment, Organization, and Functions and Responsibilities of the Grievance Hearing Body

13. Establishment of the Grievance Hearing Body

1) In accordance with Article 49(1) of Proclamation No. 1112/2011 and Regulation No. 33/2015, the Grievance Hearing Committee (hereinafter referred to as the "Committee") is hereby established under this directive.
2) The Committee shall be accountable to the head of the authority

14. Objective

The objective of the Committee is to ensure that appeals submitted regarding administrative measures taken by regulated institutions are reviewed and that legal and fair decisions are made.

15. Functions and Responsibilities of the Committee

The Committee shall have the following functions and responsibilities:

1) It shall ensure that the relevant department that took the administrative measure is informed of the grievance submitted and that a written response is provided to the grievance;
2) It shall hear, investigate, and decide on grievances submitted regarding administrative measures taken;
3) It shall request any necessary documents, evidence, witnesses, or inspection reports required to investigate and decide on the grievance;
4) The Committee shall review any grievance submitted to it in light of relevant proclamations, regulations, and directives, and issue a final decision;
5) It may uphold, amend, or modify the administrative decision and issue related orders necessary for the decision-making process. The Committee must cite

፮፥ ኮሚቴው የሰጠውን የውሳኔ ግልባጭ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ያደርጋል፤

፯፥ የሥራ ክፍሎች በሚወስዱት አስተዳደራዊ እርምጃ የሚፈጽሙትን የተደጋገመ ስህተትና ከባድ የአሠራር ግድፈት በተመለከተ አግባብ ላለው አካል የበላይ ኃላፊ ተገቢውን ምክር ይሰጣል፤

፰፥ የራሱን የአሰራር ሥነ-ሥርዓት ደንብ ያወጣል፤እና

፱፥ ከላይ የተመለከቱትን ተግባርና ኃላፊነቶች ለመተግበር አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

፲፮፥ አደረጃጀት

፩፥ ኮሚቴው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ፣ አባላት እና ፀኃፊ ይኖሩታል

፪፥ የኮሚቴው ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል አግባብ ባለው አካል የበላይ ኃላፊ ይሰየማል፡፡

፫፥ ምክትል ሰብሳቢው በአባለቱ አብዛኛ ድምጽ ይመረጣል፡፡

፬፥ አግባብ ያለው አካል የሕግ ባለሙያ የኮሚቴው ፀኃፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡

፲፯፥ የኮሚቴው አባላት አመራረጥ

፩፥ የኮሚቴው አበላት ስብጥር ከምግብና መድሃኒት ተቋማት ቁጥጥር ስራ ጋር ግንኙነት ያላቸው የስራ ክፍሎች የተውጣጡ ባለሙያዎች ይሆናል፡፡

፪፥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በኮሚቴው የሚታየውን ቅሬታ ያስከተለውን አስተዳደራዊ እርምጃ የወሰደው የሥራ ክፍል ለዚሁ ቅሬታ ምርመራ ሂደት ብቻ በአባልነት ሊሳተፍ አይችልም፡፡

፫፥ የእያንዳንዱ አባል ተጠሪነት ለኮሚቴው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

፬፥ ኮሚቴው ከአምስት ያላነሱ አባላት ይኖሩታል፡፡

፲፰፥ የሰብሳቢው ተግባርና ኃላፊነቶች

የኮሚቴው ሰብሳቢ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፦

፩፥ የኮሚቴውን ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል፤

፪፥ የኮሚቴውን አባል በቀረቡ ቅሬታዎች ላይ የቅድመ ምርመራ ተግባራትን እንዲያከናውን በመምረጥ ኮሚቴው ማጤን ያለበትን ተጨባጭ የህግ ምክንያቶች ላይ እንዲሰራ ያደርጋል፤

፫፥ ኮሚቴውን በመወከል አስፈላጊ ሲሆን አግባ ካለው አካል የበላይ ኃላፊ ጋር ግንኙነቶችን ያደርጋል፤

፬፥ ማንኛውም በኮሚቴው የሚታዩ ጉዳዮች እንደተወሰኑ ለባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባል፤

፭፥ በየ6 ወሩ አጠቃላይ ሪፖርት አጠቃላይ የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች ሪፖርት ያቀርባል፤

፲፱፥ የምክትል ሰብሳቢው ተግባርና ኃላፊነት

ምክትል ሰብሳቢው ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ሰብሳቢውን ተክቶ ይሰራል፡፡

the legal basis used to uphold, amend, or modify the decision;

6) It shall ensure that the decision is communicated to the relevant bodies;
7) It shall advise the higher authority on repeated errors and serious procedural flaws in administrative measures taken by departments;
8) It shall establish its own procedural rules; and
9) It shall perform other tasks necessary to implement the above functions and responsibilities.

16. Organization

1) The Committee shall consist of a Chairperson, Vice-Chairperson, members, and a Secretary.
2) The Chairperson of the Committee shall be appointed by the higher authority from among the members.
3) The Vice-Chairperson shall be elected by a majority vote of the members.
4) A legal expert from the relevant body shall serve as the Secretary of the Committee.

17. Selection of Committee Members

1) The members of the Committee shall be professionals drawn from departments related to the regulation of food and medicine institutions.
2) Notwithstanding sub-article (1) of this article, the department that took the administrative measure leading to the grievance may not participate in the investigation process of that grievance.
3) Each member shall be accountable to the Committee Chairperson.
4) The Committee shall have no fewer than five members.

18. Functions and Responsibilities of the Chairperson

The Chairperson of the Committee shall have the following functions and responsibilities:

1) He/she shall chair the Committee's meetings;
2) He/she shall assign pre-investigation tasks to Committee members regarding grievances and ensure that the Committee works on objective legal grounds;
3) He/she shall represent the Committee and, when necessary, communicate with the higher authority;
4) He/she shall report specific cases reviewed by the Committee to the higher authority;
5) He/she shall submit a comprehensive report every six months to the higher authority on the overall activities of departments and employees.

19. Functions and Responsibilities of the Vice-Chairperson

The Vice-Chairperson shall act in place of the Chairperson in his/her absence.

፳፡ የፀሀፊ ተግባርና ኃላፊነቶች

የኮሚቴው ጸሀፊ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩፡ ከኮሚቴው ሰብሳቢ ጋር በመመካከር የኮሚቴውን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያስተባብራል፤

፪፡ የቅሬታ ሰነዶችን፣ ቃለ ጉባኤ፣ የኮሚቴውን ውሳኔዎች እና ሌሎች ሰነዶችንም በአግባቡ መያዝን ጨምሮ ለኮሚቴው አስፈላጊ የሆኑ አስተዳደራዊ ስራዎችን በተመለከተ ድጋፍ ያደርጋል፤

፫፡ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በመቀበል ለሰብሳቢው ከማሳወቁ በፊት የአቀራረብ ፎርማሊቲዎችን ያሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም የቀረበው ቅሬታ ማሻሻያ እንዲደረግበት ሊያዝ ይችላል፤

፬፡ አስፈላጊ መስፈርቶችን ያሟሉ ቅሬታ ሲቀርቡ ይህንኑ በማረጋገጥ የቀረበው ቅሬታ በቀጥታ ለሰብሰባቢው ያሳውቃል፤ እና

፭፡ በኮሚቴው የተሰጡ ሌሎች አስፈላጊ ሀላፊነቶችን ይወጣል፡፡

፳፩፡ የኮሚቴው ስብሰባዎች

፩፡ ከኮሚቴው አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፪፡ ኮሚቴው በቀረቡ ቅሬታዎች ላይ ውሳኔ የሚሰጠው በአብዛኛው ድምጽ ሲሆን ድምጽ እኩል ለእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ድምጽ የበላይነት ይኖረዋል፡፡

፫፡ የማንኛውም የኮሚቴው አባል የተለየ ሃሳብ በውሳኔው ላይ በግልጽ ይቀመጣል፣ የኮሚቴው ጸሀፊ የሃሳብ ልዩነቶችን በአግባቡ መዝግቦ የመያዝ ኃላፊነት አለበት፡ :

፬፡ ኮሚቴው በዚህ መመሪያ መሰረት የሚቀርብ ቅሬታን ለመመርመር በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

፭፡ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቢኖርም አስተዳደራዊ እርምጃው የተቋማትን ስራ ሙሉ በሙሉ የሚያጓትት ከሆነ ሰብሳቢው ለጉዳዩ ቅድሚያ በመስጠት አስቸኳይ ስብሰባ በመጥራት በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ እንዲሰጥበት ሊደርግ ይችላል፡፡

ክፍል አራት
ስለ ቅሬታ አቀራረብ እና ውሳኔ አሰጣጥ

፳፪፡ ስለ ቅሬታ አቀራረብ

፩፡ ቅሬታ ሊቀርብ የሚችለው በባለ ፈቃዱ ወይም በተቋሙ ባለቤት ወይም በባለፈቃዱ ወይም ባለቤቱ ውክልና በተሰጠው ሰው ይሆናል፡፡

፪፡ ማንኛውም ቅሬታ በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ለአስተዳደሩ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር መቅረብ አለበት፡፡ ቅሬታዉ የቀረበለት ዋና ዳይሬክተር ለኮሚቴዉ ሰብሳቢ ይመራል፡፡ ቅሬታው የሚቀርበው ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን በኋላ ባሉ ፴ ቀናት ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

20. Functions and Responsibilities of the Secretary

The Secretary of the Committee shall have the following functions and responsibilities:

1) He/she shall coordinate regular and emergency meetings of the Committee in consultation with the Chairperson;
2) He/she shall provide administrative support to the Committee, including maintaining grievance documents, minutes, decisions, and other necessary records;
3) He/she shall receive grievances, ensure that submission formalities are completed, and, if necessary, request amendments to the grievance before informing the Chairperson;
4) He/she shall verify that submitted grievances meet the necessary criteria and directly inform the Chairperson; and
5) He/she shall perform other necessary responsibilities assigned by the Committee.

21. Committee Meetings

1) A quorum for the Committee's meetings shall be met if more than half of the members are present.
2) Decisions on grievances shall be made by majority vote. In the event of a tie, the Chairperson's vote shall be decisive.
3) Any dissenting opinions of Committee members shall be recorded in the decision, and the Secretary is responsible for properly documenting such differences.
4) The Committee shall meet once a month to review grievances submitted under this directive.
5) Notwithstanding sub-article (4) of this article, if the administrative measure significantly disrupts the operations of institutions, the Chairperson may prioritize the matter and call an emergency meeting to ensure a decision is made as quickly as possible.

Part Four:
Complaint Submission and Decision-Making

22. Complaint Submission

1) A complaint may be submitted by the concerned party, the institution's owner, or a representative authorized by the concerned party or owner.
2) Any complaint must be submitted in writing to the Director-General of the administration. The Director-General who receives the complaint will forward it to the committee chairperson. The complaint must be submitted within 30 days from the date the decision was issued.

፫፥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚቀርብ ቅሬታ ቢያንስ እርምጃ የተወሰደበት ምክንያቶች፣ ውሳኔ እና አመልካቹ አስተዳደራዊ እርምጃው አግባብነት የለውም ወይም ትክክል አይደለም የሚልበትን ምክንያቶች በዝርዝር ሁኔታ መግለጽ አለበት፡፡

፬፥ ለኮሚቴው የሚቀርብ ቅሬታ ለቅሬታው አስረጂ ይሆናሉ የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች እና ምስክር ይሆናሉ የሚባሉ ምስክሮችን ስም ዝርዝር በአባሪነት አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

፭፥ ከላይ የተገለፁትን መስፈርቶች አሟልቶ የሚቀርብ ቅሬታን ዋና ዳይሬክተር ቅሬታዉን ተቀብሎ ቅሬታው ከቀረበለት ጊዜ ጀምሮ ባሉት ከሶስት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሰብሳቢው መምራት አለበት፡፡

፮፥ በዚህ መመሪያ የተመለከቱ መስፈርቶችን ያላሟላ ቅሬታ የቀረበ እንደሆነ የኮሚቴው ሰብሳቢ የቀረበው ቅሬታ ያለበትን ጉድለቶች ለይቶ በማውጣት አቅራቢው ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ እንደገና እንዲያቀርብ በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

፯፥ ቅሬታ አቅራቢው መስፈርቶችን ያሟላ ነው የሚል ከሆነና ሰብሳቢ በአቋሙ ከፀና ቅሬታ አቅራቢው ይህንኑ በተመለከተ ያለውን አቤቱታ አግባብ ላለው አካል የበላይ ኃላፊ ማቅረብ ይችላል፡፡

፰፥ የባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ ጉዳዩን በመመርመር አግባብነት ያለውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፳፫፥ የቅሬታ ማሳወቂያ እና ምላሽ

፩፥ የኮሚቴው ሰብሳቢ የቀረበለትን ቅሬታ እርምጃውን ለወሰደው የሥራ ክፍል ካሳወቀና ቅጂውም ምክንያታዊ በሆነና ከሶስት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲደርስ ካደረገ በኋላ እርምጃ የወሰደው የስራ ክፍል በቀረበው ቅሬታ ላይ ምላሽ ከሶስት የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ እንዲያቀርብ ያደርጋል፡፡

፪፥ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚሰጥ ምላሽ ቢያንስ አቤቱታ የቀረበበትን እርምጃ ሕጋዊነት የሚያሳይ እና የቀረበው ቅሬታም አግባብነት የለውም የሚባልበትን ምክንያት የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

፫፥ እርምጃውን የወሰደው የሥራ ክፍል አግባብነት አላቸው የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎችና የምስክሮችን ዝርዝር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

፬፥ እርምጃውን የወሰደው የስራ ክፍል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት ምላሽ ሳይሰጥ ከቀረ ክፍሉ በሁለት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ እንዲሰጥ ሰብሳቢው በጽሁፍ እንደገና ሊጠይቀው ይችላል፡፡ በሰብሳቢው የሚጻፍለትን ደብዳቤንም የሥራ ክፍሉ ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ ጉዳዩ በሌለበት የሚታይ መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን በግልባጭም አግባብ ያለው አካል የበላይ ኃላፊ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

፭፥ ለሁለተኛ ጊዜ በተጻፈለት ደብዳቤ መሠረትም እርምጃውን የወሰደውና ቅሬታ የቀረበበት የሥራ ክፍል ምላሽ ሳይሰጥ የቀረ እንደሆነ ሰብሳቢው ጉዳዩ ለኮሚቴው ቀርቦ ሙሉ በሙሉ እንዲታይ ያደርጋል፡፡

3) A complaint submitted under this provision must clearly state the reasons for the action taken, the decision, and the reasons why the complainant believes the administrative action is inappropriate or incorrect.
4) The complaint submitted to the committee must include supporting documents and a list of witnesses, if any, who can substantiate the complaint.
5) If the complaint meets the above requirements, the Director-General must accept it and forward it to the chairperson within three working days from the date of submission.
6) If the complaint does not meet the requirements, the chairperson will identify the deficiencies and notify the complainant in writing to make the necessary corrections and resubmit.
7) If the complainant believes the requirements have been met and the chairperson maintains their stance, the complainant may appeal to the higher authority.
8) The higher authority will review the matter and issue an appropriate decision.

23. Complaint Notification and Response

1) The committee chairperson will notify the relevant department that took the action about the complaint and ensure a copy is delivered within three working days. The department that took the action must respond to the complaint in writing within three working days.
2) The response provided under this provision must demonstrate the legality of the action taken and explain why the complaint is deemed invalid.
3) The department that took the action must provide supporting documents and a list of witnesses, if any.
4) If the department fails to respond within the specified time, the chairperson may request a response in writing within two working days. If the department still fails to respond, the matter will be referred to the higher authority.
5) If the department fails to respond after the second written request, the chairperson will refer the matter to the committee for a full review.

፳፬፡ የቅሬታ የምርመራ ሥነ ሥርዓት እና ውሣኔ

፩፡ ኮሚቴው ቅሬታው እውነተኛና መሰረታዊ ፍሬ ነገር ከሌለው ቅሬታው ተቀባይነት የለውም ብሎ ሳለመመርመር ስልጣን ያለው ሲሆን ውሳኔውንም በጽሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

፪፡ ኮሚቴው የቀረበለትን ቅሬታ አላይም ብሎ የሚወስነው የዚህን መመሪያ አንቀጽ ፳፫ መሠረት በማድረግ ይሆናል።

፫፡ ኮሚቴው የቀረበለትን ቅሬታ መመርመር አግባብነት ያለው መሆኑን ሲወስን የውሣኔ አሰጣጡ ከዚህ በሚከተሉት ሥነ ሥርዓት መሠረት የሚመራ ይሆናል።

ሀ) ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የቀረበለት ቅሬታና መልስ መሰረት በማድረግ ጉዳዩን ለማየት በቂ ሆኖ ሲያገኘው ኮሚቴው ተከራካሪ ወገኖቹን መስማት ሳያስፈልገው የቅሬታ ማጣራት ሥራውን አከናውኖ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

ለ) ለውሣኔ አሰጣጥ ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች አስፈላጊ ሆነው ሲያገኛቸው ቅሬታ አቅራቢና እርምጃ የወሰደውን የስራ ክፍል መስማት ሳያስፈልገው ውሣኔ ይሰጣል።

ሐ) በቀረበው ቅሬታ ላይ ውሣኔ ለመስጠት አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነበት ኮሚቴው ስለተከራካሪዎቹ ከሚያውቁት ሶስተኛ ወገኖችም ማናቸውም ተጨማሪ ሠነድ ወይም ማስረጃ ሊጠይቅ ይችላል።

መ) መስማት አስፈላጊ ሲሆን ኮሚቴው ለተከራካሪዎቹ ወገኖች እና ምሥክሮች ይህንኑ ያሳውቃል። የኮሚቴው ጸሀፊምቅሬታ አቅራቢና አስተዳደራዊ እርምጃ የወሰደው ይስራ ክፍል እና ምሥክሮች ለመሰማት እንዲቀርቡ መጥሪያ ያደርሳል።

ሠ) የመሰማት ዕድል ሲሰጥ ኮሚቴው ግልጽ ያልሆኑ ነጥቦችን ግልጽ ለማድረግ ተከራካሪ ወገኖች ወይም ምሥክሮች ሊጠይቅ ይችላል።

ረ) ክርክር ላይ ያሉ ጭብጦችን ግልጽ ለማድረግ ኮሚቴው የመሰማት ሂደቱን እንደአግባቡ ሊያደርግ ይችላል።

ሰ) ኮሚቴው ጉዳዩን ከመረመረ በኂላ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 17 መሠረት ውሣኔ ይሰጣል።

ሸ) ኮሚቴው የዉሳኔ ሃሳብ ከሰጠ በኂላ የዉሳኔ ሃሳቡን ለባለስልጣኑ የበላይ ኃላፊ ያቀርባል።

ቀ) የአስታደደሩ ባለስልጣን የበላይ ኃላፊ ያጸደቀው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ መሆኑን በመግለጽ ኮሚቴው የውሣኔ ግልባጩን ለቅሬታ አቅራቢ እንዲደርሰው ያደርጋል።

፳፭፡ አስተዳደራዊ እርምጃን ለሕብረተሰቡና ለሚድያ ስለማሳወቅ

፩፡ አስተዳደራዊ እርምጃ በሕዝቡ ወይም በሚድያ እንዲታወቅ ሊደረግ የሚችለው ውሣኔ ከተሰጠበት ከ30 ቀናት በኂላ ወይም ጉዳዩ በቅሬታ አፈታት ሥነ-ሥርዓት ውስጥ ከሆነ ሂደቱ ከተጠናቀቀ ብቻ ይሆናል፡፡

፪፡ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም እርምጃን አለማሳወቅ በህብረተሰብ ጤና ላይ አደጋ ሊያመጣ ከቻለ አግባብ ባለው መንገድ እርምጃው እንዲታወቅ ያደርጋል።

24. Complaint Investigation Procedure and Decision

1) The committee has the authority to determine whether the complaint is genuine and has merit. If not, the complaint will be rejected, and the decision will be communicated in writing.
2) The committee will decide whether to accept or reject the complaint based on the provisions of Article 23 of this directive.
3) If the committee determines that the complaint warrants investigation, the decision-making process will follow the procedures outlined below:
   a) If the committee finds the complaint and response sufficient to make a decision, it may proceed without hearing from the parties involved.
   b) If additional documents are required for decision-making, the committee may issue a decision without hearing from the complainant or the department that took the action.
   c) If the committee deems it necessary, it may request additional documents or evidence from third parties.
   d) If a hearing is required, the committee will notify the parties and witnesses. The committee secretary will issue a summons for the complainant, the department that took the action, and witnesses to appear.
   e) During the hearing, the committee may ask questions to clarify unclear points.
   f) The committee may conduct the hearing process as it deems appropriate to clarify contentious issues.
   g) After reviewing the matter, the committee will issue a decision based on Article 17 of this directive.
   h) After issuing a decision, the committee will present the decision to the higher authority.
   i) The higher authority's decision is final, but the aggrieved party has the right to appeal to the appropriate court. The committee will ensure the decision is delivered to the complainant.

25. Public and Media Notification of Administrative Actions

1) Administrative actions may be disclosed to the public or media only after 30 days from the date the decision was issued or after the complaint resolution process is completed.
2) Notwithstanding sub-article (1), if withholding the action poses a risk to public health, the action may be disclosed in an appropriate manner.

፫፥ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚደረግ ማሳወቅ አግባብ ያለው አካል የበላይ ኃላፊ መፈቀድ አለበት፡፡

ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፮፥ ሪከርድን ስለመጠበቅና ማሳወቅ

፩፥ በዚህ መመሪያ መሰረት የተወሰደ ማንኛውም አስተዳደራዊ እርምጃ እርምጃውን በወሰደው የስራ ክፍል ሪከርድ ውስጥ መያዝ አለበት፡፡

፪፥ ማንኛውም አስተዳደራዊ እርምጃ በተቻለ መጠን ቁጥጥር በሚካሄድበት ተቋም መዝገብ ውስጥ አብሮ መቀመጥ አለበት፡፡ ይህ መዝገብ እርምጃውን በወሰደው የስራ ክፍል ከሌለ የእርምጃው ግልባጭ መዝገቡን ለሚይዘው የስራ ክፍል ተሰጥቶ ከመዝገቡ ጋር አንድ ላይ ተያይዞ መቀመጥ አለበት፡፡

፫፥ በዚህ መመሪያ መሰረት የተወሰደ ማንኛውም አስተዳደራዊ እርምጃ ግልባጭ አግባብ ያላቸው የስራ ክፍሎች ሁሉ ማወቅ አለባቸው፡፡

፳፯፥ ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ድንጋገጌዎች ጋር የማይጣጣም ማንኛውም መመሪያ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተካተቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

፳፰፥ መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ…………ቀን **፪ሺ፲፰** ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ዶ/ር ፅጌረዳ ክፍሌ
የድሬዳዋ አስተዳደር ጤና ቢሮ ኃላፊ

3) Any disclosure under this provision must be approved by the higher authority.

Part Five:
Miscellaneous Provisions

26. Record Keeping and Disclosure

1) Any administrative action taken under this directive must be recorded by the department that took the action.
2) Any administrative action must be recorded in a controlled institution's registry. If the department that took the action does not maintain a registry, the record must be provided to the relevant department and kept together.
3) All relevant departments must be informed of any administrative action taken under this directive.

27. Inapplicable Provisions

Any directive that conflicts with the provisions of this directive shall not apply to matters covered herein.

28. Effective Date

This directive shall come into effect starting from ………………, 2026.

Dr. Tsegereda Kifle
Dire Dawa Administration Health Bureau Head
Dire-Dawa

አባሪ 1 የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ (ቀላል ቅጣት)

Appendix 1: Written Warning (Simple Penalty)

ተ.ቁ	የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ (ቀላል ቅጣት)	ቅጣት	No.	Written Warning (Simple Penalty)	Penalty
1	የቃል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በተጠቀሰው ጊዜ ሳያሻሽል የቀረ	2500 ብር	1	Failure to comply with a verbal warning within the specified time	2,500 Birr
2	ማንኛዉም ተቋም ባለስልጣኑና አግባበብ ያላቸው አካለት ባወጡት መስፈርት ውስጥ የአስገዳጅ መስፈርቶች ጉድለት አሳይቶ ከተገኘ	3000 ብር	2	Failure to meet mandatory requirements set by the relevant authority or institution	3,000 Birr
	የምግብ ደህንነት			**Food Safety**	
3	የምግብ ንግድ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ የመንግስት በጀት ዓመት በገባ ከ3-6 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ሳያሰዳድስ የሰራ በየወሩ 500	1500 ብር	3	Food Trade Institution without renewing Competency Certificate within 3-6 months the government budget year, will be fined 500 per month	1500 Birr
4	ምግብ ንግድ ተቋም የብቃት ማረጋገጫ የመንግስት በጀት ዓመት በገባ ከ6-12 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ሳያሳድስ የሰራ በየወሩ 1000	3000 ብር	4	Food Trade Institution without renewing Competency Certificate within 6-12 months the government budget year, will be fined 1000 per month	3000 Birr
5	በአስተዳደሩ የሚመረት የታሸገ ምግብ ሳያስመዘግብ ገበያ ላይ ያዋለ	3000 ብር	5	Selling packaged food in the market without registration	3,000 Birr
6	ተፈጻሚነት ያለውን የማሸጊያ እና ገላጭ ጽሁፍ ደረጃ እና መስፈርትን የማያሟላ የታሸገ ምግብ ምርትን ለገበያ ማቅረብ	5000 ብር	6	Offering packaged food for sale that does not meet labeling and packaging standards	5,000 Birr
7	ምግብን ለፀሐይ፣ ለዝናብ፣ ለተባይ፣ ለቆርጣሚ እንሰሳ ወይም መሰል የምግብን ደህንነት ሊጎዳ ለሚችል ነገር በማጋለጥ ያስቀመጠ ወይም ለሽያጭ ያቀረበ	2000 ብር	7	Storing or displaying food in a manner that exposes it to sun, rain, dust, pests, or other conditions that may compromise food safety	2,000 Birr
8	በምግብ ተቋም በምግብ ማምረት፣ ለአገልግሎት ማዘጋጀት፣ ሽያጭ ወይም በማስተናገድ ስራ ላይ የሚሰማራ ሰራተኛውን በምግብ አማካኝነት ከሰው ወደ ሰው ከሚተላለፍ በሽታ ነፃ ስለመሆኑ ቢያንስ በየ6 ወሩ የጤና ምርመራ ሳያደረግ እንዲሰራ ያደረገ	3000 ብር	8	Allowing an employee to work in food production, preparation, service, or sales without a health check-up at least every six months	3,000 Birr
9	በምግብ ተቋም በምግብ ማምረት፣ ለአገልግሎት ማዘጋጀት፣ ሽያጭ ወይም ማስተናገድ ስራ ላይ የሚሰማራ ሰራተኛው ተገቢውን የደህንነት አልባሳት ሳይለብስ ወይም የግል ንጽህናውን ሳይጠብቅ እንዲሰራ ያደረገ 2000	2000 ብር	9	Allowing an employee to work in food production, preparation, service, or sales without wearing appropriate safety attire or maintaining personal hygiene	2,000 Birr

ተ.ቁ	የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ (ቀላል ቅጣት)	ቅጣት	No.	Written Warning (Simple Penalty)	Penalty
10	በፌዴራሉ ባለስልጣን ባልተካተተ ዝርዝር ያልተካተተን የምግብ ጭማሪ በመጠቀም ምግብን ያምረተ ወይም ያዘጋጀ 3000	3000 ብር	10	Producing or preparing food using additives not listed by the federal authority	3,000 Birr
11	በፌዴራሉ ባለስልጣን ያልተመዘገበን የጨቅላ ህጻን፣ የህጻን ተጨማሪ ምግብ፤ እና ማሟያ ምግብ ያመረተ፣ ያከፋፈለ ወይም የሸጠ	1000-3000 ብር	11	Producing, distributing, or selling infant formula, baby food, or supplementary food without registration by the federal authority	1,000-3,000 Birr
	የአልኮል መጠጥ ሽያጭ			**Alcohol Sales**	
12	ማንኛውም የአልኮል መጠጥ ከ21 አመት በታች ለሆነ ሰው መሸጥ ወይም እንዲሸጥ ያደረገ	5000 ብር	12	Selling or facilitating the sale of alcohol to a person under 21 years of age	5,000 Birr
13	የአልኮል መጠጥን በጤና ተቋም፣ ትምህርት ቤት፣ መዋለ ህጻናት፣ ዩንቨርሲቲ፣ ኮሌጅ፣ በመንግስት ተቋማት፣ በአምልኮ ቦታ፣ በስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች፣ ሲኒማ ቤቶች፣ በመንገድ ላይ እና ከአልኮል ሽያጭ ነጻ እንዲሆኑ በሚወሰኑ ቦታዎች የሸጠ	3000 ብር	13	Selling alcohol in prohibited areas such as health institutions, schools, childcare centers, universities, colleges, government institutions, places of worship, sports venues, cinemas, roads, and other designated areas	3,000 Birr
14	የአልኮል መጠጥ ማከፋፈያ ወይም ችርቻሮ ንግድ ላይ በተሰማሩ ወይም አልኮል መጠጥ ለህብረተሰብ አገልግሎት በሚያቀርብ ድርጅት ቤት ወይም ህንጻ ላይ የተቋሙን ስያሜ ለመግለጽ ህንጻ የውጭ ግድግዳ ላይ፣ በህንጻው ሌላ የውጭ ክፍል ላይ ወይም በራሱ በቆመ ማንኛውም መዋቅር ላይ የአልኮል ምርትን ሊያስተዋውቅ የሚችል ማስታወቂያ የተገኘበት ተቋም	3000 ብር	14	Displaying alcohol advertisements on the exterior walls or other external parts of a building or structure where alcohol is distributed or sold	3,000 Birr
	የመድኃኒት እና የህክምና መሳሪያ			**Medicine and Medical Equipment**	
15	በይዞታው ስር የሚገኝ መድኃኒት ጥራቱ፣ ደህንነቱ፣ ፈዋሽነቱ ጥራቱ፣ ደህንነቱ፣ እና ውጤታማነቱን በሚያጓድል መልኩ ያከማቸ፣ ያጓጓዘ እና የሸጠ ወይም ለአገልግሎት ያቀረበ	ከ2000-5000 ብር	15	Storing, transporting, selling, or providing medicine that compromises its quality, safety, efficacy, or effectiveness	2,000-5,000 Birr
16	የህክምና መሳሪያ ጥራቱ፣ ደህንነቱ፣ እና ውጤታማነቱን በሚያጓድል መልኩ ያከማቸ፣ ያጓጓዘ እና የሸጠ ወይም ለአገልግሎት ያቀረበ	ከ3000-5000 ብር	16	Storing, transporting, selling, or providing medical equipment that compromises its quality, safety, or effectiveness	3,000-5,000 Birr
17	የፌዴራሉ ባለስልጣን ባወጣው መመሪያ መሰረት የችርቻሮ ሽያጭ ዋጋ ያልተለጠፈበትን ወይም ያልተፃፈበት መድኃኒት የሸጠ	2000 ብር	17	Selling medicine without a price tag or label as required by federal authority guidelines	2,000 Birr

ተ.ቁ	የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ (ቀላል ቅጣት)	ቅጣት	No.	Written Warning (Simple Penalty)	Penalty
18	ናርኮቲክ እና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒቶች፣ የነዚህ መድኃኒቶች መዝገብ እና የማዘዣ ወረቀቶች ቁልፍ ባለው በቀላሉ ሊሰበር ወይም ሊንቀሳቀስ በማይችል ሳጥን ውስጥ ወይም በተለየ ክፍል ውስጥ ቆልፎ ያለስቀመጠ	ከ2000-3000 ብር	18	Failing to store narcotic and psychotropic drugs, their records, and prescription forms in a secure, locked, and immovable container or separate room	2,000-3,000 Birr
19	የመደኃኒት ቅመማ አገልግሎት የሚሰጥ መደኃኒት ቤት የመደኃኒት ቅመማ በተመለከተ የአሰራር ስራዓት ሳይኖረው የሰራ	2000 ብር	19	Operating a pharmacy without proper procedures for drug compounding	2,000 Birr
20	የመድሃኒት ቅመማ አገልግሎት በሚመለከት የእያንዳንዱን የመደኃኒት ቅመማ ወይም የተጠቃሚውን የተሟላ መረጃ አለመያዝ	ከ1000-2000 ብር	20	Failing to maintain complete records of drug compounding or user information	1,000-2,000 Birr
21	የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀቱ የሚጠይቃቸውን መረጃዎች በትክክል ሳያሟሉ ያዘዘ ወይም ያደለ	ከ1000-2000 ብር	21	Issuing or prescribing a medication without accurately completing the required information on the prescription form	1,000-2,000 Birr
22	የፀረ-ተህዋሲያን መድኃኒቶች በአንድ የመድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ላይ አንድ ወጥ የህክምና አሰጣጥ ሥርዓት ከሚፈቅደው መጠን ውጪ ያዘዘ ወይም ያደለ	ከ3000-5000 ብር	22	Prescribing or administering antibiotics beyond the permitted dosage on a single prescription form	3,000-5,000 Birr
	የውበት መጠበቂያ ምርት			**Cosmetic Products**	
23	በአስተዳደሩ ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ ሳያገኝ እና ሳይመዘገብ የውበት መጠበቂያ ያመረተ	5000 ብር	23	Producing cosmetics without obtaining certification or registration from the relevant authority	5,000 Birr
24	በአስተዳደሩ ባለስልጣን የብቃት ማረጋገጫ ሳያገኝ እና ሳይመዘገብ የውበት መጠበቂያ ማማከፋፈል ወይም በመቸርቸር ስራ ላይ የተሰማራ	1000-2000 ብር	24	Distributing or selling cosmetics without obtaining certification or registration from the relevant authority	2,000 Birr
25	በሸቀጣሸቀጥ ችርቻሮ ተቋም የውበት መጠበቂያ ምርትን ከሌሎች ሸቀጦች ሳይለዩ እና በህግ የሚጠየቁ መስፈርቶችና ሳያሟሉ ከተለያዩ ሸቀጣሸቀጥ ምርቶች ጋር በችርቻሮ ተቋም መሸጥ	ከ1000-2000 ብር	25	Selling cosmetic products in retail establishments without separating them from other products or meeting legal requirements	1,000-2,000 Birr
	የትምባሆ እና ተያያዥ ምርቶች አስተዳደር			**Tobacco and Related Products Administration**	
26	የትምባሆ ልዩ ፍቃድ ሳያሳድስ የመንግስት በጀት ዓመት በገባ ከ6-12 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ የሰራ የትምባሆ ችርቻሪ በየወሩ 500	500-1500	26	Without renewing special tobacco retail permit within 6-12 months of the government budget year, will be fined 500 per month	500-3000 Birr
27	የትምባሆ ልዩ ፍቃድ ሳያሳድስ የመንግስት በጀት ዓመት በገባ ከ6-12 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ የሰራ የትምባሆ አከፋፋይ በየወሩ 2000	2000-12000 ብር	27	Without renewing special tobacco wholesale permit within 6-12 months of the government budget year, will be fined 500 per month	2000-12000 Birr

ተ.ቁ	የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ (ቀላል ቅጣት)	ቅጣት	No.	Written Warning (Simple Penalty)	Penalty
28	ማንኛውም ሰው የተከለከለ ይዘት ያለውን ትምባሆ ወይም በህገ ወጥ መንገድ የገባን የትምባሆ ምርት ወይም ሺሻ ወይም የኤሌክትሮኒክ ኒኮቲን መስጫ መሣሪያን ወይም ሌላ ከሲጋራ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ለኒኮቲን መስጫ የሚያገለግል የቴክኖሎጂ ምርት በችርቻሮ የሸጠ	2000 ብር	28	Selling tobacco products containing prohibited substances, illegally imported tobacco products, or electronic nicotine delivery devices in retail establishments	2,000 Birr
29	ለህዝብ ክፍት በሆነ ማንኛውም ቦታ፣ ከበር መልስ ባለ ማንኛውም የስራ ቦታ፣ የትራንስፖርት መጠበቂያ ቦታ በሁሉም የህዝብ መጓጓዣ እና በጋራ መኖሪያ ቤት ማንኛውም የጋራ መገልገያ እና የስራ ቦታዎች በአስር ሜትር ዙሪያ ውስጥ ያጨሰ ወይም የተጠቀመ	1000 ብር	29	Smoking or using tobacco in public places, workplaces, transportation hubs, or within 10 meters of public areas	1,000 Birr
30	እድሜው ከ21 ዓመት በታች ለሆነ ሰው የትምባሆ ምርትን መሸጥ ወይም ከ21 ዓመት በታች በሆነ ሰው እንዲሸጥ ያደረገ	1000 ብር	30	Selling tobacco products to a person under 21 years of age or facilitating such a sale	1,000 Birr
31	ትምባሆ መሸጥ በተከለከለበት አከባቢ የሸጠ ወይም በተቋሙ የትምባሆ ምርት የተገኘበት	1000-3000 ብር	31	Selling tobacco products in prohibited areas or where tobacco products are found in the establishment	1,000-3,000 Birr
32	የተከፈተ ፓኬት ሲጋራ ወይም በፍሬ የሸጠ	1000 ብር	32	Selling open-packaged cigarettes or loose cigarettes	1,000 Birr
33	በፌዴራል ባለስልጣኑ የሚወሰነውን የጤና ማስጠንቀቂያ መልዕክትና ስዕል ያልያዘ የትምባሆ ምርት በችርቻሮ መሸጥ	1000-3000 ብር	33	Selling tobacco products in retail without the health warning message and image as determined by the federal authority	1,000-3,000 Birr
34	ትምባሆ ማጨስ፣ መጠቀም ወይም መሸጥ በተከለከለበት አከባቢ፣ ማጨስ የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ ጽሁፍ እና ተጓዳኝ ሥዕል ካልለጠፈ ወይም ሲጨስ አስፈላጊውን እርምጃ ካልወሰደ	1000 ብር	34	Smoking, using, or selling tobacco in prohibited areas without displaying the required warning text and image or taking necessary measures	1,000 Birr

አባሪ 2 ከባድ ቅጣት (የብቃት ማረጋገጫ ወይም ልዩ ፈቃድ ወይም ዕውቅና ወይም ምዝገባ ምስክር ወረቀት ዕገዳ የሚያሰጥ)

Appendix 2: Severe Penalties (Involving Suspension of Competency Certification, Special Permit, Recognition, or Registration Certificate)

ተ.ቁ	ከባድ ቅጣት (የብቃት ማረጋገጫ ወይም ልዩ ፈቃድ ወይም ዕውቅና ወይም ምዝገባ ምስክር ወረቀት ዕገዳ የሚያሰጥ)	ቅጣት	No.	Severe Penalty (Involving Suspension of Competency Certification, Special Permit, Recognition, or Registration Certificate)	Penalty
1	ቀላል ቅጣት ተላልፎበት በድጋሚ የፈፀመ የቀላል የገንዘብ ቅጣቱን እጥፍ እና የ5 ቀን እገዳ		1	If a minor penalty is repeated, the fine is doubled, and a 5-day suspension is imposed.	
2	ማንኛንም የታሸገ ምግብ ደረጃውን ያልጠበቀ ወይም ያስተሻሽግ ጉድለት እንዲኖረው በማድረግ ወይም አስመስሎ በመስራት ያመረተ፣ ያከማቸ፣ በጅምላ ያከፋፈለ ወይም በችርቻሮ የሸጠ ወይም በማንኛውም መንገድ ለኅብረተሰቡ አገልግሎት ያቀረበ፣ እንዲሰራጭ ያደረገ እንደሆነ	ከ3000-10000 ብር	2	Producing, storing, distributing in bulk, or selling any packaged food that does not meet standards, is defective, or is counterfeit.	3,000-10,000 Birr
3	የታሸገም ሆነ ያልታሸገ ምግብ ለህብረተሰብ አገልግሎት ደህንነቱ ሳይጠበቀ እንዲሁም አሳሳች በሆነ መንገድ ያቀረበ	ከ3000-5000 ብር	3	Providing unpackaged or packaged food to the public without ensuring safety or in a hazardous manner.	3,000-5,000 Birr
4	የምግብ ተቋም ምግቡን ለብክለት በሚያጋለጥ ሁኔታ እና ተፈጻሚነት ያለውን የደህንነት መስፈርቶች ሳያሟላ ምግብ ያመረተ፣ ለአገልግሎት ያዘጋጀ፣ ያጓጓዘ እና የሸጠ	5000 ብር እና ከ5-15 ቀን እግድ	4	A food establishment producing, preparing, transporting, or selling food without meeting safety standards or in conditions that promote contamination.	5,000 Birr and 5-15 days suspension
5	በዓድ ነገር የተቀላቀለበት ምግብ ሲሸጥ ወይመ ለአገልግሎት ሲያቀርብ የተገኘ	ከ5000-10000 ብር እና ከ10-15 ቀን እግድ	5	Selling or serving food mixed with foreign objects.	5,000-10,000 Birr & 10-15 days suspension
6	የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቁ፣ የተበላሹ፣ ተገቢው የጥራትና ደህንነት መስፈርት የማያሟላ፣ ትክክለኛ የስርጭት ሂደትን ተከትሎ ያልመጣ ወይም ህገ-ወጥ ምግብ በተቋም ውስጥ ለሽያጭ ያዘጋጀ ወይም የሸጠ	5000-20000 ብር እና 15 ቀን እግድ	6	Preparing or selling expired, spoiled, substandard, or illegally distributed food in an establishment.	5,000—20,000 Birr and 15 days suspension
7	አግባብ ባለው አካል እንዲበለጽግ የተወሰነ ምግብን መበልጸግ በሚገባው ሁኔታ ያልበለፀገ ያመረተ፣ ያከፋፈል ወይም የሸጠ	ከ10000-20000 ብር	7	Producing, distributing, or selling food that should have been properly sterilized but was not.	10,000—20,000 Birr
8	የመጠጥ ውሃ ወይም የታሸገ ውሃ ወይም ሌላ ለመጠጥ የሚውል ውሃ አቅራቢ ወይም አምራች ውሃው በብሄራዊ ደረጃ የተቀመጠ የደህንነት ደረጃ ሳያሟላ ያቀረበ	ከ10000-20000 ብር	8	Providing drinking water or packaged water that does not meet national safety standards.	10,000—20,000 Birr

ተ.ቁ	ከባድ ቅጣት (የብቃት ማረጋገጫ ወይም ልዩ ፈቃድ ወይም ዕውቅና ወይም ምዝገባ ምስክር ወረቀት ዕገዳ የሚያስጥ)	ቅጣት	No.	Severe Penalty (Involving Suspension of Competency Certification, Special Permit, Recognition, or Registration Certificate)	Penalty
9	የመጠጥ ውሃ ለንግድ አገልግሎት የሚያቀርብ ድረጅት በባለስልጣኑ ሳይመዘገብ ለንግድ አገልግሎት ያዋለ	3000 ብር	9	A drinking water provider operating without registering with the relevant authority.	3,000 Birr
10	የተቋም ብቃት ማረጋገጫ ሳያወጣና በአስተዳደሩ ባለስልጣን ሳይመዘገብ በምግብ ንግድ የተሰማራ ወይም የብቃት ማረጋገጫውን ከአንድ የመንግስት በጀት ዓመት በላይ ሳያሳድስ የቀረ	2000-5000 ብር	10	Engaging in food trade without obtaining a competency certification or registering with the administration.	2,000—5,000 Birr & 5 days
11	የአልኮል መጠጥን ለማስተዋወቅ በነፃ መስጠት፤ የዋጋ ቅናሽ እንዳለ መግለጽ፤ አልኮል ለተጠቀመ ሰው ለሌላ አገልግሎት የከፈለ፤ ስጦታ የሰጠ፤ ሽልማት እንዲተገበር ያደረገ ተቋም	ከ5000-20000 ብር	11	Promoting alcohol by offering free samples, price discounts, or gifts to consumers.	5,000—20,000 Birr
12	የአልኮል መጠጥ በህዝብ መሰብሰቢያና መገልገያ ቦታ፣ በስፖርት ማዘውተሪያ፣ ትምህርት ቤት፣ የመንግስት ተቋም፣ በማንኛውም መንገድ ላይ፣ ባዛር፣ ገበያ ማዕከል፣ ወጣት ማዕከል በጋራ መኖሪያ ቤቶች እና መሰል ህዝብ በሚሰበሰብበት ቦታ አልኮልን ማስተዋወቅና ፕሮሞት ያደረገ	50000 ብር	12	Introducing or promoting alcohol in public gathering places, sports venues, schools, government institutions, markets, youth centers, or shared residential areas.	50,000 Birr
13	በማንኛውም ህንጻ የውጭ ግድግዳ ላይ፣ በህንጻው ሌላ የውጭ ክፍል ላይ ወይም በራሱ በቆመ ማንኛውም መዋቅር ላይ የአልኮል ምርትን ሊያስተዋውቅ የሚችል ማስታወቂያ ያኖረ ወይም እንዲኖር ያደረገ ማስታወቂያ አስነጋሪ	50000 ብር	13	Displaying alcohol advertisements on the exterior walls of buildings or other outdoor structures.	50,000 Birr
14	የአልኮል ምርት ለማስተዋወቅ ማጓጓዣን ጨምሮ በማንኛውም የህዝብ መጓጓዣ ትራንስፖርት አካል ላይ ከድርጅቱ ዓርማ ባለፈ የአልኮል ምርት ስዕል፣ አልኮልን ለማስተዋወቅ የሚችል መልዕክት ወይም ሌላ አልኮልን ሊያስተዋውቅ የሚችል ተያያዥ መግለጫን የለጠፈ ወይም ያስቀመጠ ማስታወቂያ አስነጋሪ	50000 ብር	14	Placing alcohol advertisements on public transport vehicles, including logos, images, or messages promoting alcohol.	50,000 Birr
15	የአልኮል መጠጥን ከሎተሪ እጣ ወይም ከሽልማት ጋር በማንኛውም መንገድ በማያያዝ ማስተዋወቅ እና ሽያጭ የሰራ ማስታወቂያ አስነጋሪ	50000 ብር	15	Promoting alcohol through lotteries, prizes, or similar methods.	50,000 Birr
16	አልኮልን በቢልቦርድ አማካኝነት የሚደረግ የማስተዋወቅ ተግባር የፈፀመ 100000	100000 ብር	16	Conducting alcohol promotion activities using billboards.	100,000 Birr
17	ለአስተዳደሩ ባለስልጣን ሣያሳውቅ በይዞታው ስር የሚገኝን መድኃኒት ወይም የህክምና መሳሪያን ከሚፈቀደው የንግድ ሰንሰለት ዉጭ ያስተላለፈ	ከ25000-40000 ብር	17	Transferring medicine or medical equipment outside the authorized supply chain without notifying the relevant authority.	25,000—40,000 Birr

ተ.ቁ	ከባድ ቅጣት (የብቃት ማረጋገጫ ወይም ልዩ ፈቃድ ወይም ዕውቅና ወይም ምዝገባ ምስክር ወረቀት ዕገዳ የሚያስጥ)	ቅጣት	No.	Severe Penalty (Involving Suspension of Competency Certification, Special Permit, Recognition, or Registration Certificate)	Penalty
18	ማንኛውም ሰው ከአስተዳደሩ ባለስልጣን ልዩ ፈቃድ ሳያገኝ የትምባሆ ምርት ያመረተ ወይም በጅም ያከፋፈለ	50000	18	Producing or distributing tobacco products without a special permit from the relevant authority.	50,000 Birr
19	በመድኃኒት ወይም በህክምና መሳሪያ ተቋም ከመድኃኒት ወይም ከህክምና መሳሪያ ምርት ዝግጅት ጋር ግንኙነት ያለውን ባለሙያ በሙያው የተመዘገበ ስለመሆኑ ወይም የታደሰ ሙያ ስራ ፍቃድ የያዘ መሆኑን እና ስራዉን ለመስራት ብቃቱ ያለው መሆኑን ሳያረጋገጥ እንዲሰራ ያደረገ ወይም የቀጠረ ተቋም	ከ10000-20000 ብር	19	Hiring a professional without verifying their qualifications or registration in the field of medicine or medical equipment.	10,000—20,000 Birr
20	የመድኃኒት ወይም የህክምና መሳሪያ ችርቻሮ ድርጅት መድኃኒትን ወይም የህክምና መሳሪያን በጅምላ የሸጠ	ከ30000-50000 ብር እና ከ1-3 ወር እግድ	20	A retail medicine or medical equipment establishment selling in bulk.	30,000-50,000 Birr and 1-3 months suspension
21	ከተፈቀደለት ደረጃ በላይ መድሃኒት ዓይነት በላይ በጤና ተቋም ወይም የመድሃኒት ተቋም ይዞ የተገኘ	ከ10000-30000 ብር	21	Possessing medicine in excess of the permitted quantity in a health or medical institution.	10,000-30,000 Birr
22	በህግ በልዩ ሁኔታ ከተፈቀደ ውጭ ማንኛውንም መድኃኒት ተፈጻሚነት ያለውን የጥራት፣ የደህንነት እና ፈዋሽነት መስፈርት የማያሟላ ወይም ያልተመዘገበ መድኃኒት ለሽያጭ ማቅረብ	ከ20000-50000 ብር	22	Offering for sale any medicine that does not meet quality, safety, or efficacy standards or is unregistered.	20,000-50,000 Birr
23	ተፈጻሚ የሆኑ መስፈርቶችን ሳይከተል የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድኃኒት ወይም ፕሪከርሰር ኬሚካል ያከፋፈለ፣ ያከማቸ፣ ያጓጓዘ፣ የያያዘ ወይም የሸጠ	25000 እና 1-3 ወር እግድ	23	Distributing, storing, transporting, or selling narcotic or psychotropic drugs or precursor chemicals without following regulations.	25,000 Birr and 1-3 months suspension
24	ለአገልግሎት የሚቀርብ ማንኛውም የህክምና መሳሪያ የጥራት፣ ደህንነት እና ውጤታማነት መስፈርት የማያሟላ ወይም ያልተመዘገበ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም ለአገልግሎት ያዋለ	ከ20000-50000 ብር	24	Offering for sale or service any medical equipment that does not meet quality, safety, or efficacy standards or is unregistered.	20,000-50,000 Birr
25	የመድኃኒት ወይም የህክምና መሳሪያ ተቋም በመድኃኒት ወይም የህክምና መሳሪያ ንግድ ስራ ላይ በአስተዳደሩ ባለስልጣን ሳይመዝገብ እና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያገኝ የሰራ	ከ30000-50000 ብር	25	Operating a medicine or medical equipment business without registering with the relevant authority or obtaining a competency certificate.	30,000-50,000 Birr

ተ.ቁ	ከባድ ቅጣት (የብቃት ማረጋገጫ ወይም ልዩ ፈቃድ ወይም ዕውቅና ወይም ምዝገባ ምስክር ወረቀት ዕገዳ የሚያሰጥ)	ቅጣት	No.	Severe Penalty (Involving Suspension of Competency Certification, Special Permit, Recognition, or Registration Certificate)	Penalty
26	ማንኛውም ሰው ባለሙያ ሳይሆን መድኃኒትን፣ የህክምና መሣሪያን ወይም ተያያዥ ምርትን የሸጠ፤ ባለሙያ ባልሆነ ሰው እንዲሸጥ ወይም እንዲቀርብ ያደረገ እንደሆነ ከብር አሥር ሺ. እስከ ብር አንድ መቶ ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡	ከ10000-100000 ብር	26	Any person selling medicine, medical equipment, or related products without being a qualified professional, or enabling such sales.	10,000-100,000 Birr and
27	አዋጁን እና ደንቡን እና ለማስፈጸም በሚወጣ ህግ በመጻረር የማዘዣ ወረቀት ሳይኖር ወይም ከተፈቀደው ውጭ በሆነ የማዘዣ ወረቀት መድሃኒት የሸጠ፣ የሰጠ፣ ያደለ ወይም ያዘዘ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር አምስት ሺ. እስከ ብር ሃምሳ ሺ. በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡	ከ5000-50000 ብር እና 10-30 ቀን እግድ	27	Selling, distributing, or prescribing medicine without a proper prescription or beyond the authorized scope.	5,000-50,000 Birr and 10-30 days suspension
28	የመድኃኒት ወይም የህክምና መሳሪያ ተቋም ንግድ ስራ ላይ ያለ የመንግስት በጀት ዓመት በገባ በሶስት ወር ጊዜ ውሰጥ ሳያሳደስ የሰራ 5000 እና ከ6-9 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ሳያሳድስ የሰራ 15000	ከ5000-15000 ብር	28	A medicine or medical equipment establishment operating without renewing its license within the specified period.	5,000—15,000 Birr
29	የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቁ፣ የተበላሹ፣ ተገቢው የጥራትና ደህንነት መስፈርት የማያሟላ፣ ትክክለኛ የስርጭት ሂደትን ተከትሎ ያልመጣ ወይም ህገ-ወጥ መድኃኒት በተቋም ውስጥ የያዘ፣ ያደለ ወይም የሸጠ	25000 ብር ቅጣት እና ከ10 ቀን -1ወር እግድ	29	Holding, distributing, or selling expired, spoiled, substandard, or illegally distributed medicine in an establishment.	25,000 Birr and 10 days-1 month suspension
30	የትምባሆ ኢንዱስትሪ ጣልቃ ገብነትን ስለመከላከል በደንቡ አንቀፅ 41 የተቀመጠውን ድንጋጌ የተላለፈ	50000 ብር	30	Violating the provisions of Article 41 of the regulation on preventing interference in the tobacco industry.	50,000 Birr
31	ሲጋራ እና ሺሻን ጨምሮ ማንኛውንም ዓይነት የትምባሆ ምርት በንግድ መልክ ወይም ከሌላ አገልግሎት ጋር በማያያዝ በክፍያ ወይም በነጻ ያቀረበ ወይም እንዲጨስ ያደረገ	ከ20000-50000 ብር	31	Offering any type of tobacco product, including cigarettes and shisha, for sale or free distribution.	20,000—50,000 Birr
32	የተከለከለ ይዘት ያለውን ትምባሆ ወይም በህገ ወጥ መንገድ የገባን የትምባሆ ምርት ወይም በፌዴራል ባለስልጣኑ የሚወሰነውን የጤና ማስጠንቀቂያ መልዕክትና ስዕል ያልያዘ የትምባሆ ምርት ወይም ሺሻ ወይም የኤሌክትሮኒክ ኒኮቲን መስጫ መሣሪያን ወይም ሌላ ከሲጋራ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ለኒኮቲን መስጫ የሚያገለግል የቴክኖሎጂ ምርት ያመረተ፣ ያከፋፈለ፣ ያከማቸ፣ ያጓጓዘ እና በጅምላ የሸጠ	50000 ብር	32	Producing, distributing, storing, transporting, or selling prohibited tobacco products, shisha, or electronic nicotine delivery devices without health warnings.	50,000 Birr

ተ.ቁ	ከባድ ቅጣት (የብቃት ማረጋገጫ ወይም ልዩ ፈቃድ ወይም ዕውቅና ወይም ምዝገባ ምስክር ወረቀት ዕገዳ የሚያስጥ)	ቅጣት	No.	Severe Penalty (Involving Suspension of Competency Certification, Special Permit, Recognition, or Registration Certificate)	Penalty
33	በአዋጅና ደንብ ውስጥ የተካተተ የህፃናት ማሟያ ወተትን አስመልክቶ የወጣ ማስታወቂያ የተላለፈ	ከ 10000-20000 ብር	33	Violating advertising regulations related to infant formula.	10,000—20,000 Birr
34	በፌዴራል ባለስልጣኑ ጥቅም ላይ እንዳይውል የተከለከለ የውበት መጠበቂያ ምርት ለንግድ አገልግሎት ያዋለ	ከ5000-10000 ብር እና 15 ቀን እገዳ	34	Using prohibited cosmetic products for commercial purposes.	5,000—10,000 Birr and 15 days suspension
35	የቁጥጥር መስፈርቶችን የማያሟላ የውበት መጠበቂያ ምርት ወይም ተፈጻሚነት ባለው መስፈርት መሰረት ከተፈቀደ የንጥረ-ነገር ይዘት መጠን በላይ ያለው ወይም የተከለከለ ይዘት ያለው የውበት መጠበቂያ ምርት እና ጥሬ ዕቃ ማምረት፣ ማከፋፈል ወይም መሸጥ	ከ10000-20000 ብር እና 15 ቀን እገዳ	35	Producing, distributing, or selling cosmetic products that do not meet control standards or contain prohibited substances.	10,000—20,000 Birr and 15 days suspension
36	የትምባሆ ልዩ ፍቃድ ሳይኖረው ትምባሆ ምርት የቸረቸረ	3000 ብር	36	Retailing tobacco products without special permit	3000 Birr
37	የትምባሆ ልዩ ፍቃድ ሳይኖረው ትምባሆ ምርት የቸረቸረ	10000	37	Retailing tobacco products without special permit	3000 Birr